የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት (ኢብስመ)።
Ethiopian NATIONAL Government In Exile (ENGIE)
Mailing Address: 2901W Parker Road #864631 Plano, Texas
Email: ethiopianngovie2005gmail.com Phone Number: 214-642-0394

Ethiopian National Government In Exile, was founded on September 15, 1986
In Dallas Texas

Dallas, Texas USA
October 16, 2018

አቶ በቀለ ገርባ እና አምስቱ የኦሮሞ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠየቁ የቀረበ ሁለተኛ ደብዳቤ ደብዳቤ።

በቅድሚያ ይድረስ ለአቶ በቀለ ገርባ።
ለአቶ ፍሬው ኢብሳ (ዳውድ)።
ለአቶ ዮሐንስ ለታ (ሌንጮ)።
ለአቶ ዲማ ነገዎ ።

በመጀመርያ ፡ የእግዚአብሄር ሰላምታ ይድረሳችሁ እንላለን።

ደብዳቤያችን እና ጉዳዩ፥

ደብዳቤ በኦክቶበር 15 እ.አ.አ. ማልት በትናትንታው እለት የጻፍንላችሁ እንዳለ ሆኖ ፡ የአምስቱንም ድርጅቶቻችሁን ስም ዝርዝር ያካተተ እና ጥቂት ማብራሪያን ያካተተ ደብዳቤ መልሰን መላክ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘነው ከዚህ በታች ሁለተኛው ደብዳቤያችን ይድረሳችሁ እንላለን።

አቶ በቀለ ገርባ በአንተ አማካኝነት በመስከረም 14 ቀን 2011 ፡ በአምስት የኦሮሞ ግንባሮች ስም ማለትም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ OLF)፡ የኦሮሞ ፌድራስሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ OFC)፡ የተባበሩት ኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ UFIO)፡ የኦሮሚያ ነፃነት አንድነት ግንባር (OLFU)፡ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ODF)ማለትም አንተ በምክትል ፕሬዘደንትነት  የምትመራውን ድርጅት ኦፌኮን ጭምሮ ፡ አቶ ዲማ ነገዎ በተገኘበት ፡ በጋራ ስምምነት መግለጫ በሚል ፡ በሕዝብ ብዛት 75% በሆነው ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በሕብረት ፡ የታሪክ ክህደት በመፈጸማችሁ ይሄውም ፡ አዲስ አበባን የኦሮሞ ብቻ ሃብት ናት ፡ በታሪክም በሕግም ፡ በሚል ያነበብከውን መግለጫ እና በአንድነት ያስተጋባችሁትን አዋጅ ፡ በሕግም ቦታ የሌለው እና በታሪክም በእርግጠኝነት የምንነግራችሁ ያልነበረ መሆኑን እያስታወቅን ፡ አዋጃችሁ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውድቅ መሆኑን ልናሳውቃችሁ እንወዳለን። ከታሪክ ውጪ ያቀረባችሁትን አዲስ አበባ ጥንትም አሁንም የኦሮሞ ነች የሚለው የአፍ ታሪክ ኦሮሚያ አገር ነው ብላችሁ በማጣመር ያወጃችሁትን የፈጠራ ታሪክ እና

የአዲስ አበባ ከተማ ባለቤትነት አዋጃችሁን የኢትዮጵያ ብሔራዊ የስደት መንግስት በጥብቅ ያወግዛል። ወድቅም አድርጉታል።

እንደሚታወቀው ዛሬ እናንተ አምስታችሁ የድርጅት መሪዎች በአዲስ አበባ ከተማ ንዋሪውን መጤ እና ሰፋሪ በሚል የኮነናችሁት ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ82 ብሄር በላይ ከሆነው እና ካለው አብራክ የተወለደ ነው። አንዱም ብሄር በታሪኩ ከጎረቤት አገሮች ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ተስፋፍቶ የሚኖር መጤ እና ሰፋሪ ሳይሆን ፡ የጥንታዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሁኑ በታሪክ ተቀምጦ የሚገኝ ነው። ሆንም እናንተ በመስከርም 14 ቀን በ2011 የጥንታዊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማለትም ፡ የአዲስ አበባ እና የመላው ኢትዮጵያ ባለቤት የሆነው መጤ እና ሰፋሪ ፡ አገር የሌለው ጥገኛ አድርጋችሁ በማስቀመጣችሁ ፡ በታሪክም በሕግም በቅርብ የሚያስጠይቃችሁ ትልቅ ወንጀል ከመሆኑም በላይ በአንድ አገር ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ላይ (በ81 ብሄር ላይ ) የኦሮሞ ሕዝብ ተወካይ እራሳችሁን አድርጋችሁ በተለመደው ፡ በኦሮሞ ሕዝብ ስም ክህደት ፈጽማችሁበታል። በመሆኑም ጥፋታችሁን አምናችሁ እና ተጸጽታችሁ ለይቅርታ ጊዜው እንዳልረፈደባችሁ ተግነዘባችሁ ፡ የጫራችሁት እሳት በበለጠ እየተቀጣጠለ ከመምጣቱ በፊት ባስቸኳይ የመላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማለትም የኦሮሞውን ሕዝብ ጭምር (በጥቅሉ 82ብሄር )ትልቅ ይቅርታ እንድትጠይቁት በጥብቅ እንጠይቃችኋልን ።

ኢትዮጵያ ፡ ከመላው (82 ብሄር) የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ በተወለድንው በአንድነትዋ እና በዳር ድንበሯ ላይ በማንደራደረው ሴቶች እና ወንዶች ልጆችዋ ተከብራ እና ታፍራ ለዘለዓለም ትኑር።

የሐረርወርቅ (የኢትዮጵያወርቅ) ጋሻው

መስራች እና ፕሬዘደንት።